# የጉንፋን ክትባት
# ዘንድሮ የበለጠ ጠቃሚ ነዉ



**ከምን ግዜዉም የበለጠ ዘንድሮ የጉንፋን ክትባት ማግኘት ጠቃሚ ነዉ።** ለ ኮቪድ-19 ክትባት ላይኖረን ይችላል፤ ሆኖም ግን ከ50 ዓመታት በላይ በሰላም በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ሰዎች ሲሰጥ የኖረ የጉንፋን ክትባት አለን። የጉንፋን ክትባቱ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት ከመታመም ሊጠብቃችሁ ይችላል። ያ ደግሞ ዶክተር ቢሮና ሆስፒታሎች ከመሄድ ይጠብቃችኋል፤ በተጨማሪም ጠቃሚ የሕክምና ግብዓቶችን ለኮቪድ-19 ታማሚዎች እንድንቆጥብ ይረዳናል።



**ማንኛዉም ከ 6 ወር ዕድሜ ያለፈ ሰዉ የጉንፋን ክትባት በየዓመቱ ማግኘት አለበት።** በተለይ እንደ ለጋ ህጻናት ና ነፍሰ ጡር የሆኑት፣ ከ65 ዓመት በላይ የሆኑ አዋቂዎች፣ ወይንም አንዳንድ የጤና ሁኔታዎች እንደ አስም፣ የልብ በሽታ ና ስኳር ያለባቸዉ ሰዎች ያሉ በጣም ከፍተኛ ስጋት ላይ ላሉ ቡድኖች በጣም ጠቃሚ ነዉ። ወሳኝ ሠራተኞች ና የጤና እንክብካቤ ሠራተኞችም ከብዙ ሰዎች ስለሚገናኙ ክትባት ማግኘቱ ጠቃሚ ነዉ።



**የቀረነዉ ሰዎች ለጉንፋን ስንከተብ፣ በማህበረሰባችን ዉስጥ የበለጠ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎችን እንድንጠብቅ ይረዳናል።** ታዳጊ ልጆችና ህጻናት፣ በዕድሜ የገፉ ኣዋቂዎች፣ ና ነፍሰ ጡር የሆኑ ሴቶች በጉንፋን የመታመም ዕድላቸዉ ከፍ ያለ ነዉ። በጉንፋን ከተያዙ ሆስፒታል የመተኛትና የመሞት የበለጠ ስጋት አለባቸዉ። ሁላችን ከተከተብን ጉንፋን ወደ ቤተሰባችን፣ ጓደኞቻችን፣ እና ጎረቤቶቻችን እንዳይሰራጭ ይረዳል።



**በኮቪድ ወረርሽኝ ወቅት እንኳ ደህንነትዎን ጠብቀው የጉንፋን ክትባት ማግኘት ይችላሉ።** የጉንፋን ክትባት ከዶክተር ቢሮ፣ የማህበረሰብ ጤና ማዕከል፣ መድኃኒት ቤት ወይንም የመኪና ድራይቭ ስሩ ክሊኒክ በሰላም ማግኘት ይችላሉ። የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ደንበኞችን ከኮቪድ-19 ለመጠበቅ ተጨማሪ እርምጃዎችን እየወሰዱ ነዉ። የጉንፋን ክትባት ለመዉሰድ ሲሄዱ ራስዎንና ሌሎችን መጠበቃቸውን ያረጋግጡ፡ ሁሌም ቢያንስ ስድስት ጫማ መራቅ፣ ማስክ መልበስ፣ እና ቤት ሲደርሱ እጅዎን በደንብ ይታጠቡ። ማንኛዉም ዓይነት የህመም ምልክት ካለዎት እባክዎን ክትባትዎን ለማግኘት እስከሚሻልዎት ድረስ ይጠብቁ።



**ኪንግ ካዉንቲ ዉስጥ ባሉ በርካታ ጣብያዎች የጉንፋን ክትባት በነጻ ይቀርባል።** ኢንሹራንስ ከሌለዎት ወይንም ለክትባት መክፈል ካልቻሉ በዚህ ወቅት ብዙ በነጻ ክትባት የሚሰጥባቸዉ ኩነቶች አሉ። አንዳንዶቹ ቀጠሮ እንዲይዙ ይጠይቃሉ። አንዳንዶቹ በመኪና ሆኖ (ድራይቭ-ስሩ) ወይንም በእግር የሚኬድባቸዉ ኩነቶች ናቸዉ። የክትባት ክሊኒክ ግዜና ቦታ ኣስመልክቶ ኣዲስ መረጃ በየግዜዉ የጉንፋን ወቅት እስኪወጣ በ www.kingcounty.gov/findaclinic ላይ ይቀርባል።

Public Health
Seattle & King County